የሰ/መ/ቁ. 55078

ታህሣሥ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግል ማህበር

**ተጠሪዎች -** 1. አሸናፊ አለሙ

2. በለጠ እሸቱ

3. አብዮት ጉግሳ

4. ወንድወሰን ጌቱ

5. አባይነህ ደምሴ

6. ሰሎሞን ይገዙ

7. ኤልያስ አክመል

8. ሳህሌ ከበደ

9. እንግዳ ደበሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ አቋርጦብናል በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪዎች ያለበቂ ምክንያት ከሥራ በመቅረታቸው ነው በማለት ተከራክሮአል ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት በመቅረታቸው ምክንያት ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ከተደረጉ በኃላ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር መመዝገባቸው ትክክል አይደለም በማለት አመልካች መከራከሩን ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ በአመልካች የቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲያገኙ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ እነሱ ሳይጠይቁ የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዙን በማንሳት እነሱንም በመጨመር ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት እንደውሣኔው እፈጽማለሁ በማለት የአመልካች ጠበቃ ተጠሪዎች ግን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡

በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በዝርዝር ተመልክተናል በእርግጥም ከሣሾች ሆነው በፍ/ቤቱ መዝገብ የተመለከቱት ዘጠኙም ተጠሪዎች ቢሆኑም ክርክሩ ሊሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት የቀረቡት ግን 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች እንደሆኑ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን ሁኔታ በመገንዘብ እንደዚሁም የአመልካች ጠበቃ ያቀረበውን አቤቱታ በመስማት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን /ተከሣሾችን/ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎ እንደነበር ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ በአንድ በኩል የሆነው የክርክሩ ሂደት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን በማንሳት ተጠሪዎቹ በክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር ቀሪውን የክርክር ሂደት አጠናቆ ውሣኔ እንደሰጠ ተገንዝብናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 73 በተደነገገው መሠረት ትዕዛዝ ሰጥቶ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎአል ከዚህ በኃላ ተጠሪዎቹ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በማድረግ የወሰነው ደግሞ ጉዳዩን ቀጥሎ ባለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ /ቁ 74/ ከተቀመጠው ሥርዓት ውጪ በሆነ ሁኔታ እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪዎቹ እነሱን በተመለከተ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው አላመለከቱም ከሁሉ በላይ ደግሞ ተጠሪዎቹ በየግላቸው ከአመልካች ጋር ባላቸው የሥራ ውል መሠረት ክርክር አልተደረገም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪዎቹ የክርክሩ ተካፋይ እንደሆኑ አድርጎ በመወሰኑ ውሣኔው ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አተገባበርም ሆነ ለውሣኔው መሠረት ሊሆን የሚገባውን ፍሬ ነገር ከመጨበጥ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13664 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 83507 የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ እንዲፈጽም አይገደድም በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ